የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ
TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: ezanareg@hotmail.com

# <u>ድርድር ካልተቀበለ ፤ ሰላማዊ ህዝባዊ ዓመፅ ይግጠመው</u> !

አምባገነኑ ኢህአዴግ ከ3 ወራት በህዋላ በግንቦት ወር እንደለመደው የተጭበረበረ ምርጫ ለማካሄድ ዝግጅቱን አጠናቅቆ የአሸንፋለሁ ድንፋታውን ተያይዞት ይገኛል ። ዛሬ ራሱ የሚቆጣጠረው ምርጫ ቦርድና የምርጫ ሕግ አዘጋጅቶ የፈለገ ያጅበኝ ያልፈለገ ደግሞ "መንገዱን ጨርቅ ያርግለት" እያለን እንደሆነ አሳምሮ ይገባናል ። ነጻና ገለልተኛ ባልሆነ በዚሁ ምርጫ ቦርድና ሕግጋቱ የሚከናወነው የምርጫ ትያትር ኢህአዴግ አሸናፊ ነኝ ብሎ እንደሚወጣ የማይገነዘብ ፖለቲካዊ ኃይል ይኖራል ብለን ለመገመት ያዳግተናል ። ኢህአዴግ በራሱ ፕሮግራም ብቃት የሚተማመን፤ በህዝባዊ ሥልጣን የበላይነት የሚያምን ቢሆን ኖሮ የምርጫ ቦርድና ሕግጋቱ ነጻና ገለልተኛ ይሁን የሚለውን ተቃዋሚ ኃይሎች ያቀረቡት ዴሞክራሲያዊ ጥሪ ለማስተናገድ አሻፈረኝ ባላለ ነበር ። በድርጅታዊ ብቃቱ፡ በፕሮግራሙና በመራጩ ህዝብ ላይ የማይተማመን፤ ተራ ቡድናዊ ጥቅሞችን ከማስከበር በላይ ሊሄድ የማይችል ድርጅት በመሆኑ ዴሞክራሲያዊ ህዝባዊ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ እንደማይችል ደጋግሞ በተግባር አሳይቶናል ። ይህ ቡድን አስቀድመን እንደምናውቀው ቅንጣት ታክል ሃገራዊነትና ህዝባዊነት ስለሌለው ቀዳሚ አጀንዳው ሥልጣን ላይ መቆየት በመሆኑ የቀጣዩ ምርጫተብየ መደምደምያም የድርጅቱ መሠረታዊ ባህሪ መግለጫው እንደሚሆን ኣይሳትም።

ኢህአዴግ ብቻውን የፈጠረው የምርጫ ቦርድና ህግጋቱ ለራሱ ለኢህአዴግ ብቻ እንዲያገለግል ሆኖ የተቀናጀና የተዋቀረ መሆኑ ከጅምሩ ቢታወቅም፤ ባለፈው የምርጫ~ተብየው ሽርጉድ ውጤቱን በሚገባ በተግባር አይተነዋል። በብዙ አከባቢ ህዝቡ የወከላቸውና ብዙ መከራ ችሎ የመረጣቸው እጩዎቹ ሲገደሉ፥ ሲታፈኑና እስር ቤት ሲወረወሩ፤ ህዝቡ የተፋቸው ኣስመሳዮች ደግሞ ተኪዎች ተበለው የፓርላማ ወንበር ሲሰጣቸው ዓይን የማያየው ጉድ የለምና አይተናል ። ኣቤት የሚባልበት ይሁን ፍትሕ የሚገኝበት የሕግ የበላይነት ተቓም ስለሌለ "አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ " እንዲሉ ህዝቡ ግፉንና በደሉን ተሸክሞ እንዲቀር ተገደዋል። አሁንም ቢሆን የምርጫ ሥርዓት ኣድማሳዊነት፤ ሕጋዊነትና መብት አንስተው የሚከራከሩ ወገኖች ከእስራት፥ ከግርፋትና ከግድያ አልዳኑም። የኢህአዴግ የፀጥታ ኃይል በዚህ የዓፈና ሥራ ተሰማርቶ ቀጣዩም "ምርጫ" በኢህአዴግ አሸናፊነት እንዲፈጸም ሀገሩን በጠቅላላ እያተራመሰው እንደሚገኝ ይታወቃል ።

ከዚህ በተጨማሪም ምርጫውን ለመቆጣጠር የሚያስችለው በመንግሥታዊ መዋቅር ስም ከላይ እስከ ታች እያንዳንዱ ቤተስብ ድረስ የሚዘልቅ መረብ ዘርግተዋል ። ከቀበሌ እንኳ ብንጀምር ወደታች 3 ደረጃ የወረዱ እርከኖች ተዋቅረው እናገኛለን ። እነሱም 1ኛ. የንኡስ ቀበሌ 2ኛ. ጎጥ 3ኛ. መንግሥታዊ ቡድን ናቸው ። እያንዳንዱ ቀበሌ እንደስፋቱ በ3 ወይም 4 ንኡስ ቀበሌ፤ እያንዳንዱ ንኡስ ቀበሌ በ5 ጎጥ፤ እያንዳንዱ ጎጥ 30 የሚሆኑ ቤተሰቦች በሚይዝ መንግሥታዊ ቡድን ተደራጅተው አስፈላጊውን መመሪያ እየተቀበሉ እንዲፈጽሙ ይገደዳሉ ። በዚህ ላይ የዛሬው የቀበሌ ሹመኛ ተቀጥሮ የሚሠራ የኢህአዴግ ጉዳይ አስፈጻሚ ባለ ደመዎዝ ነው ። የሚከፈለው ደመዎዝ የህዝብ ገንዘብ ቢሆንም ቀጣሪው ኢህአዴግ በመሆኑ ደሞዙ እንዳይቀርበት በምርጫው ወቅትም ኢህአዴግን የሚያገለግል ሰው ነው። በያንዳንዱ እርከንም 3 የአመራር አባላት ተመድበው

ተጠያቂነታቸው ከበላያቸው ላለው አካል ሆኖ ከቀበሌው እንቅስቃሴ ተጠቃሚዎች ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው ።

ይህ እስከ ቤተሰብ ድረስ የዘለቀው መዋቅር በትግራይና በአማራ ክልሎች ከተዘረጋ ቆይቷል ። ለልማት ሥራ በሚል ሽፋን በሌሎች ክልሎችም እንዲዘረጋ ተደርጓል ። ለልማት የሚል ሽፋን ይሰጠው እንጂ ዋናው ዓላማው ህዝቡን ለመቆጣጠር የተዘረጋ ማሌሊታዊ መዋቅር ነው ። ህዝቡ እንደሆነ ይቅርና ሊለማ የዕለት ጉርሱን አጥቶ በእርዳታ ከሚኖሩ ህዝቦች አንዱ ሆኖ ለመገኘቱ ራሱ የኢህአዴግ ዓመታዊ የልመና ዘገባ ያስረዳል ።

የምርጫ ቦርዱ መዋቅር አላይ ከተገለጸው ቤተሰብ ድረስ ከዘለቀው መዋቅር ጎን ለጎን ተቀናጅቶ የኢህአዴግ የምርጫ ትያትርን ያስፈጽማል ። ይህ ቡድን የኢህአዴግ ተወካይ እንዲመረጥ ህዝቡን ያስገድዳል ፤ ማስገደድ ባልቻለበት ከተማዎችም የምርጫ ሳጥኖቹን ገለባብጦ ኢህአዴግ አሸነፈላቹህ ያለና አሁንም ሊለንም ራሱን ያዘጋጀ ቡድን ነው። የኢህአዴግ ተመራጭ እንኳንና አሁን ድሮም ቢሆን በገለልተኛ ቦርድ አማካይነት ነጻ ምርጫ ከተካሄደ አንድም የሚመርጠው ህዝብ እንደሌለ አሳምሮ ያውቃል። ስለዚህም በነዚህ በቀጠራቸው ወገኖችና በምርጫ ቦርዱ አማካይነት አሸንፌአለሁ ብሎ ለሌላ የ5 ዓመታት የዓፈና አገዛዝ እንደተዘጋጀ አያጠራጥርም ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነን 3 ወራት የቀረው የኢህአዴግ የምርጫ ትያትር እንዴት መመልከት ይገባል? ምን ዓይነት እርምጃስ መወሰድ አለበት? ብሎ መጠየቅና መልሱንም መሻት የማንም ሃገሩ የሚወድ ዴሞክራት ሃላፊነት ይመስለናል። እንደ ት.ዴ.ት የመሰሉ ድርጅቶች በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊያን ኃይሎች ሕብረት (ኢዴኃሕ) አገሪቱ በሰላማዊ መንገድ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንድትሸጋገር ህዝቡም የሚፈልገውን አስተዳደራዊ ሥርዓት መርጦ እንዲያቋቁም ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ ተመሥርቶ ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ እናካሂድ ካለ እንሆ ሁለት ዓመት ሆኖታል። ይህም በጉልበት ሳይሆን በሰላም በድርድር እንዲፈጸም ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል።
አሁንም ጥረቱን አላቋረጠም ።

ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ ተመሥርቶ ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ቢካሄድ ኢምንት ታክል የህዝብ አመኔታ የሌለው የመለስ መንግሥት ከያዘው ሥልጣን እንደሚወገድ አሳምሮ በማወቁና በጉልበት ከያዘው ሥልጣን ላለመልቀቅ "ምርጫ ቦርዱን ነፃና ገለልተኛ አላደርግም፥ ሕገ ደንቡንም አልቀይርም" በማለት የህዝቡና የብዙኃኑ ፖለቲካዊ ፓርቲዎች ሕጋዊና ገንቢ ጥያቄን አጣጥሎ ሀገሪቱን ወደ ከፋ ቀውስ እየገፋት ነው። እስካሁን በተከናወነው ድርድርም መሠረታዊ ያልሆኑ ጉዳዮችን ለማጭበርበር ያህል አስተካክላለሁ ይበል እንጂ ምርጫውን ነፃና ፍትሐዊ የሚያደርጉ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ ላለማድረግ መወሰኑ ግልጽ እየሆነ መጥቷል። ሀገሪቱ ብትደቅም ብትበታተንም ጉዳዩ ያልሆነ አምባገነናዊ አገዛዝ ለዚህ ገንቢ ድርድር ጀርባውን ቢሰጥ ምን ያስደንቃል !

እንግዲህ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ በተከለከለበት፣ የህዝብ ድምፅ እንዲሰማና ወሳኝ እንዲሆን በማይፈለግበት፣ የግለሰብ አምባገነንነት ባንሰራራበት፣ የአገሪቱ የመከራ ዘመን እንዲቀጥል የሚያደርግ የምርጫ ሂደት ውስጥ መሳተፍ ጥቅሙ ምንድነው? ለማንነው? የሚሉትን ጥያቄዎች አያይዘን ለማንሳት እንገደዳለን። ይህ ቁልፍ ጉዳይ በምናነሳብት ወቅት፡ በመሠረቱ ለፖለቲካ ሥልጣን የሚወዳደሩ የፖለቲካ ኃይሎች በአንድ የምርጫ ሂደት ውስጥ የሚሳተፉበት ዓላማን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል ። ይኸውም

1ኛ. ፕሮግራሙን ይዞ መራጩ ህዝብ ፊት በመቅረብ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር እኩል ተወዳድሮ የብዙኃኑን ድምጽ በማግኘት ለማሸነፍና አገሪቱን የመምራት ኃላፊነት ለመሸከም ፡

2ኛ. በተለያዩ ምክንያቶች ምርጫውን ለማሸነፍ እንደማይቻል ቢታወቅም ዴሞክራሲያዊ ሂደትን ለማጎልበትና ለማስፋት እንዲሁም የፕሮግራሙ ደጋፊዎች ድምጽ የመስጠት

መብት ለማስጠበቅ ሲባል መሳተፍ ተገቢ ይሆናል ።

ይሁን እንጂ እነዚህ ተሳትፎዎች ተግባራዊ በሚያደርግ ዴሞክራሲያዊ አሠራር ላይ ካልተመረኮዙ በራሳቸው ምንም ትርጉም የሚሰጡ አይደሉም። ከላይ የተጠቀሱት ሁለት የምርጫ ዓላማዎች ውጤት እንዲኖራቸው ለማድረግ ከተፈለገ በመጀመርያ ደረጃ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘት የግድ ይላል ። እነሱም ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ እንዲሁ በጥቅሉ ስናስቀምጣቸው አንድን ምርጫ ነፃና ፍትሓዊ ነው ሊያሰኙት የሚችሉ ኣድማሳዊ መስፈርቶች መሟላትን ይጠይቃል። ከነዚህ ውስጥ ገለልተኛ የምርጫ ቦርድና የጋራ ሕገደንብ መኖር በወሳኝነቱ የሚጥቀስ ይሆናል። ይህ ገለልተኛ አካል ሳይፈጠርና ሁሉንም እኩል የሚያስተናግድ የጋራ ሜዳ ሳይበጅ የሚካሄድ ምርጫ ምርጫ ሊባል አይችልም ብቻ ሳይሆን የምርጫን ትርጉም ማዛባትን ያስከትላል። ከዚህም በተጨማሪ ህዝቡ ለመሠረታዊ ለውጥ እንዳይታገልና ኣመርቂ እድገት እንዳያስመዘግብ በተድበሰበሰ ሂደት ተወስኖ እንዲቀር በማድረግ ህዝባዊ ተሳትፎን የሚያደናቀፍ ይሆናል ። በአሁኑ ሰዓት ኢህአዴግ ምርጫውን ዴሞክራስያዊ የሚያደርግ ድርድር ኣልቀበልም ብሎ ብቻውን ተቆጣጥሮታል። ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የሉም ። ህዝቡና ሕብረቱ የጠየቁትን ኣድማሳዊ የምርጫ መስፈርቶች ሳይረጋገጡ "ምርጫ" ውስጥ የሚገቡ ወገኖች ምርጫውን ማሸነፍ እንደማይችሉ ወይም በሌላ አነጋገር አሸናፊ ቀድሞ በታወቀበት ጨዋታ ውስጥ መግባታቸው እንዳለፈው የአምባገነኑ የኢህአዴግ የምርጫ ትያትርን ከማጀብና ሕጋዊ ሽፋን ከመስጠት ያለፈ የሚያመጡት ትርጉም እንደማይኖር ቢገነዘቡት። ከወዲሁም በኢህአዴግ መመረጥ ሊከተል ከሚችለው ጥፋት፤ አገሪቱን ለማዳን ለሚደረገው ትግል ከፍተኛ ኣሉታዊ ተጽእኖ እንደሚኖረው መታወቅ ይኖርበታል። በዚህ ምርጫ ተብየ ትያትር ኢህአዴግ "ባሸናፊነት" ሲወጣ አሁን እያናፈሰው እንዳለው ከ70_80 ፓርቲዎች ጋር ተወዳድሬ አሸነፍኩ እያለ ቡራ ከረዩ ማናፋቱ ብቻ ሳይሆን ኣጥፊ ፖሊሲዎቹ ሲያንሰራራ የሚያስከትሉት ጠባሳ ከፍተኛ ግንዛቤ ማግኘት አለበት ። ይህ ማለት ለምሳሌ 'ከኤርትራ ጋር ለመታረቅ ባለ 5 ነጥብ የሰላም ሓሳብ በማቅረቤ ስታወግዙኝ የነበረው ይኸው ታየ ! ህዝቡ ይህንን ውሳኔ ባቋም ደረጃ መውሰዴን ያውቃል። ይህንን እያወቀም መርጦኛልና። ህዝባዊ ውክልና አለኝ' በማለት ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ አስቀድሞ የጀመረውን የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለኤርትራ አሳልፎ መስጠትን ሕጋዊ ያደርገውና 'እኔ ምን ላድርግ፥ ህዝቡ የመረጠኝ ይህንን አቋሜን እያወቀ ነው' እንደሚለን መታወቅ አለበት። በዚህም አያበቃም ሑሞራን አስመልክቶ ከሱዳን መንግሥት ጋር የጀመረው ድርድርም የኢትዮጵያን ሉዓላዊ መሬት ለሱዳን በማስረከብ እንደሚያጠናቅቀው ከወዲሁ ግንዛቤ ማግኘት አለበት።

ከሱዳንና ከኤርትራ ላለው ችግር ህዝቡ የጠየቀውን መፍትሄ እያኮላሸ፥ ኣሁን ደግሞ ሃገራዊ ስሜት ያለው ለመምሰልና በምርጫው ላይ ለተቀሰቀሰው ተቃውሞ ለማቀዝቀዝ በኣባይ ላይ ከግብጽ ጋር የቆየው ኣጀንዳ ከፍቶብናል። ሌሎች ከባድ ክህደቶችም መጥቀስ ይቻላል። እንግዲህ ኣድማሳዊ መስፈርቶች ሳይማሉ፥ ይህ ሃገሪዊነት የሌለው መንግስት ባቀናጀው የምርጫ ትያትር እንዲሁ መሳተፍ የተጠቀሱት ችግሮች እንዲያንሰራሩና ሕጋዊነት ከማላበስ በስተቀር እርባናው የቱ ላይ ነው።

እዚህ ላይ እንግዲህ የምናካሂደው ትግል ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታ ነው ካልን ይህንን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ የምንችለው ከኢህአዴግ ጋር አብረን ኢ_ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ውስጥ በመሳተፍ ሳይሆን የዴሞክራሲያዊ ምርጫ ክስተትን እውን ለማድረግ በምናደርገው የከረረ ህዝባዊ ትግል ብቻ ነው። ትግላችን ውጤቱ ኣስቀድሞ በታወቀና ለውጥ በማያመጣ "ምርጫ" መሳተፍ ሳይሆን፤ ህዝባችን የሚፈልገውን የመምረጥ መብት ለማስከበርና ህዝቡም ለዚሁ ወሳኝ ግብ እንዲበቃ ማነሳሳትና ማደራጀት ቁልፉ ጥያቄ መሆኑ መታወቅ አለበት ።

ይህን ማድረግ የሚቻለውም ከአሁን ጀምሮ የኢ.ህአዴግ የማጭበርበር ዘዴን ያለ ምህረት በጋራ በማጋለጥ ብቻ ነው ። ይህንን በጋራ በማድረግ ህዝባችንንና አገራችንን ከሌላ የ5 ዓመት የኢ.ህአደግ የመከራ አገዛዝ ነፃ ለማድረግ እንዲቻል በኢ.ህአዴግ ከተዋቀረው የተጭበረበረ ምርጫ ራስን ነፃ ማድረግና ዘላቂ መፍትሔን መሻት፥ ህዝባችንንም ለዚህ ግብ ማዘጋጀት ከሁሉም ዴሞክራሲያዊ ኃይላት ተግባራዊ አስተዋጽኦ ይጠበቃል። የሃገሪቱን ዘግናኝና አሳፋሪ ሁኔታ የተረዳ ፖለቲካዊ ድርጅት ሁሉ 4 ወይም 5 የፓርላማ ወንበር ማግኘቱ ሳይሆን ላገሪቱ ዘላቂ መፍትሔ የሚያስገኝ የትግል አቅጣጫ መያዝ ዋናው ስትራተጂ ማድረግ ይጠበቅበታል ። ለውጥ የማያመጣ ድምጽ ይዞ ፓርላማ ውስጥ መቀመጥ ብሎም በመለስና በካድሬዎቹ እንደባይተዋር እየተቆጠሩ መኖር በራስም ሆነ በሃገሪቱ ላይ  ፖለቲካዊ ጥፋት ማድረስ ነው ።

ሀገራችን ካለችበት ዘግናኝና አሳፋሪ ሁኔታ የምትገላገለው ኢ.ህአዴግ ተወግዶ ህዝቡ የሚቆጣጠረው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲመሠረት ብቻ መሆኑ ከሚገባው በላይ ተደጋግሞ ተገልፀዋል ። ይህ ወሳኝ የመፍትሔ አቅጣጫ ለመያዝ መረባረብ ከሁሉም ዴሞክራሲያዊ ኃይል የሚጠበቅ የትግል ዘዴ ነው ። ህዝቡ ኢ.ህአዴግን መልሶ ወደ ሥልጣን በሚያወጣ የምርጫ ሂደት መሳተፉን አቁሞ ፥ ይህ ዓፋኝ አገዛዝ የሚወገድበት ሰላማዊ ህዝባዊ ዓመፅ እንዲያነሳ መቀስቀስ ፥ ማደራጀትና መምራት የሁሉም አገር ወዳድ ዴሞክራት ተቀዳሚ ሥራ መሆን አለበት ። አለዚያ ሀገራችን ባለችበት ዘግናኝና አሳፋሪ ሁኔታ የጋራ መስፈርቶቹ ሳይሟሉ እንደገና ሌላ 5 ዓመት ለማስቀጠር የተቀነባበረው የኢ.ህአዴግ ምርጫ ተብየ~ትያትር ውስጥ ተዋናይ ሆኖ መገኘት ህዝቡ ወሳኙ መፍትሔ ላይ እንዳይደርስ ማደናገር መሆንኑ እንዲታወቅ ይገባል ።

ሁለት ዓመታት በፈጀው ድርድር ምርጫ ቦርዱንና ሕገ~ደንቡን ገለልተኛ በማድረግ ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ማካሄድ በሚል ሓሳብ ላይ ከኢ.ህኣዴግ ጋር ስምምነት ላይ መድረስ አልተቻለም ። ለምርጫ ትያትሩ በቀሩት 3 ወራት ውስጥ ደግሞ ኢ.ህአደግ ጭፍን አምባገነናዊ እምነቱን ይቀይራል ማለት ዘበት ነው። በዴሞክራሲና ኣምባገነንነት መካከል ያለው ልዩነት ያክል በህዝቡና በኢ.ህኣዴግ መካከል ስላለ ነው። ይህንን ጠንቅቆ ያወቀው የተምቤንና የመቀሌ ህዝብ ባምባገነኖች ምርጫ ኣንሳተፍም ብሎ ቀድሞ ተነስቶ እየታገለ ነው፡፡ ወቅቱ ሶሊዳሪቲ_ትግራይ እንዳስተጋባው 'ህዝባዊ እምቢታን' የሚጠይቅ ሆኖዋል። በዚህ አምባገነናዊ ምርጫ~ተብየ ሂደት ገብቶ ህዝቡን መቀስቀስ፥ ማደራጀትና ለሰላማዊ ህዝባዊ ዓመፅ ማዘጋጀት አንዱ ትክክለኛ የትግል ዘዴ ሲሆን ፤ የኣራዳዎች ምርጫን እንደ ወሳኝ ምእራፍ ቆጥሮ ኢ.ህአዴግ የሚለግሠውን የፓርላማ ወንበር ለማግኘት መራወጡ ለአምባገነኖቹ ህጋዊ እውቅና ማጎናፀፍና ባገራችንና ህዝባችን ላይ የወረደውን መከራ እንዳለ እንዲቀጥል ማድረጉ ስለሚሆን ከዚህ ትልቅ ፖለቲካዊ ስሕተት መቆጠብ ያስፈልጋል። የዴሞክራቶችና ሀገር ወዳድ ኃይሎች ትግል እርባና የሚኖረው ህዝቡ ከአፋኝ አምባገነኖች ተገላግሎ ፥ ያለምንም ስጋትና ጥቃት ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ለማካሄድ ሲበቃና ስለሆነ ለዚህ የሚያስችለውን መነሳሳት ፥ መደራጀትና ሰላማዊ ህዝባዊ ዓመፅ ኣሁንኑ ይቀጣጠል። የዴሞክራሲያዊ ስርኣት ግንባታ እውን የሚሆነው ሂደቱ በዚህ ሲጀምር ነው ።

ድርድር የማይገባው ዓመፅ ይገጥመዋል ! ! !
አምባገነኖቹ በህዝቡ ትግል መወገዳቸው አይቀርም ! ! !
ሰላምና ዴሞክራሲ ሰፍኖ ኢ.ትዮጵያ ታብባለች ! ! !

ት.ዴ.ት    የካቲት 1997 ዓ.ም